# የኢትዮጵያውያን ማሕበር በሆላንድ

## Vereniging van Ethiopiërs in Nederland
## Ethiopian community in The Netherlands

## “ሐይማኖት ነገድ ወይም ዘር የለውም!”

ከኢትዮጵያውያን ማሕበር በሆላንድ የተሰጠ ወቅታዊ የአቋም መግለጫ

ጥር 23 ቀን 2015ዓ ም (10-02-20223)

በአገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት 32 ዓመታት የሰፈነው የፖለቲካ ሥርዓት እጅግ በጣም ኋላቀር በሆነ የጎሰኝነት ጽንሰ ሃሳብ የሚመራ በመሆኑ የአገራችንን አንድነትና የሕዝቧንም አብሮነት ከአደጋ ውስጥ አስገብቷል። በተለይም ላለፉት 5 ዓመታት በአቢይ አህመድ አሊ እጅግ ኃላፊነት የጎደለው፣ ደካማና ጨካኝ አመራር የተነሳ በአገሪቷ ላይ የደረሰው ውድቀትና በሕዝቧ ላይ ያስከተለውና አሁንም የቀጠለው ስቃይ፣ እንግልትና ወከባ ተዘርዝሮ የማያልቅና በቃላት ለመግለጽ የሚያስቸግር ነው።

“ሌባ ሲሰርቅ ይተባበራል፤ ሲካፈል ይጣላል” እንዲሉ ከአሳዳጊው ከሕወሃት ላይ የቀማውን የስልጣን ወንበር ጠቅልሎ ለመያዝ እንዲያመቸው በሸረበው ሴራና ተንኮል የተነሳ ለሁለት ዓመት በዘለቀው የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ንፁሃን የአገራችን ዜጎች ዓላማ ለሌለው ከንቱ እልቂት ተዳርገዋል። ግምቱ በብዙ መቶ ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል። ከ2 ሚሊዮን ሰው በላይ ከመኖሪያው ቦታው ተፈናቅሏል። ከ20 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ለከፋ ችግር፣ ለረሃብና ለበሽታ ተጋልጧል። ህፃናትን ያላሳዳጊ፤ እናቶችንና አዛውንቶችን ያለጧሪ በማስቀረት ለመከራ ተዳርገዋል።

ይህ ጎጠኛና ጨካኝ አገዛዝ ዋና ዓላማው የአገሪቱን የአንድነት እሴቶች የሆኑትን ሁሉ በማፈራረስ ኦሮሚያ የሚለውን አገረ መንግስት እውን ለማድረግ ስለሆነ፤ ለአገሪቱ አንድነትና ለሕዝቧ አብሮነት ድርና ማግ የሆኑትን የእምነት ተቋማትና የማህበረሰብ ክፍሎች በማዳከምና ከቻለም ከምድረ ገጽ ለማጥፋት እጅግ ተግቶ በመስራት ላይ ነው።

በተለይም በአማራውና በኢትዮጵያዊነታቸው በፍፁም በማይደራደሩትን ማሕበረሰቦች በአብሮነትና በሰላም ሕዝቡን አቀራርበው ባኖሩት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና የእስልምና እምነች ተቋማት ላይ ከመቼውም ጊዜ በከፋ ደረጃ የጥፋት ሰይፉን ስሎና መዝዞ በመነሳት ለማቀጣጠል እየጣረ ያለው የሠደድ እሳት እንዴ ከተነሳ አደጋው እራሱን ጭምር እንደሚያወድመውና የጋራ አገራችንንም አንድነት በእጅጉ ሊያናጋ እንደሚችል የማስተዋል ህሊናው በማን አለብኝነትና በእብሪት ጭንብል ስለተጋረደ በፍፁም የተገነዘበው አይመስልም።

የእብሪቱም ጥሩ ማሳያ ባለፈው ጥር 14 ቀን 2015 (22-01-2023) ዓ ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ከፍተኛ አካል ከሆነው ሲኖደስ ዕውቅና ውጪ በሕገ-ወጥ መንገድ 26 ኤጲስቆጶሳትን በድብቅ በመሾም ያደረገው እጅግ በጣም ኃላፊነት የጎደለው ሙከራው ጥሩ ማረጋገጫ ነው።

በመሆኑም ይህችን የአገር ዋልታና ማገር የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስትያን ለሁለት ለመሰንጠቅ የተደረገውን አደገኛ ሙከራ እና ከዚህ ጋርም ተያይዞ ሊከሠት የሚችለውን አደገኛ ሁኔታ አስመልክቶ የኢትዮጵያውያን ማህበር በሆላንድ (ኢማሆ) በመላው ኔዘርላንድ ውስጥ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባደረገው አስቸኳይ ሕዝባዊ የስብሰባ ጥሪ መሠረት ተገቢውን ምላሽ በመስጠት፤ እኛ የሀገራችን ሁኔታ በእጅጉ ያሳሰበን ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተከታታይ ውይይቶችን በማድረግ በጉዳዩ ዙሪያ በዝርዝርና በጥልቀት ከተወያየን በኋላ የሚከተለውን ባለ 12 ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ከፍተኛ አካል ከሆነው ከቅዱስ ሲኖደስ ዕውቅና እና ከቀኖናዋ ውጭ በሕገ-ወጥ መንገድ በድብቅ ኢጲስ ቆጶሳትን የመሾም ሂደት አጥበቀን እየተቃወምን፤ የቅዱስ ሲኖዶሱ አስቸኳይ ስብሰባ አድርጎ ያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች ሙሉ በሙሉ እንደግፋለን።

2. በእምነት አባቶችና በምዕመናኑ ላይ የሚደርሰውን መንግሥታዊ አፈና እና ወከባ አጥብቀን እናወግዛለን። ይህ በመንግስት የተደገፈ የአሸባሪነት ተግባር በአስቸኳይ እንዲያቆምም አጥብቀብ እናሳስባለን።

3. የአብይ አህመድ መንግስት የመጨረሻው መጀመሪያ የሆነውን በቤተ አምነቶች የውስጥ አሰራርና የእምነት ነጻነትን የማወክ አስነዋሪና አደገኛ ተግባር ሲከናወን የጸጥታ አካሉ የድርጊቱ ተባባሪና አስፈጻሚ ሁነው መገኘታቸው፤ ከሁሉም በላይ እጅግ በጣም አሳዝነኖናል። አስቆጥቶናል። ይህን እስነዋሪ ድርጊታቸውንም በጥብቅ እናወግዛለን፡፡

4. ይህን እኩይና አፍራሽ ተግባሩንም ለዓለም ማህበረሰብም ለማሳወቅ ባለንበት አገርና በአውሮፓ ደረጃ ለማጋለጥ ተግተን እንደምንሠራም ቁርጠኝነታችንን እንገልጻለን።

5. ለአገሪቱ አንድነት ድርና ማግ የሁኑትን የኦርቶዶክስ ተዋህዶንና የእስልምና እምነትን ከፋፍሎ ለማባላት ያደረገውንና በማድረግም ላይ ያለውን ሙከራም አጥብቀን እናወግዛለን።

6. በስማቸው የሚነገድባቸው ማህበረሰቦች በተለይም የትግራይና የኦሮሞ ተወላጆች ከህወሃትና ከኦነጋውያን መዳፍ ለመውጣትና ከእልቂት አዙሪት ለመዳን ከቀረው ወገናቸው ጋር የቆዩ አብሮናታቸውንና የትልቅ አገር ኢትዮጵያ ባለቤትነታቸውን በሚያረጋግጥላቸው ሕዝባዊ ትግል እንዲሳተፉ ለማሳሰብ እንወዳለን።

7. በአገር ውስጥና በውጭ ያለው የማህበረሰብ ክፍልና የሲቪክ ማህበራት በሙሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና የእስልምና እምነት ተቋማት የጋራ ሕብረት በመፍጠር በተለይም በየቦታው በግፍ ከሚጨፈጨፈው ከአማራው ማህበረሰብ ጎን እንዲሰለፉ ጥሪ እናቀርባለ።

8. የመከራው ጠንሳሽና ባለቤት የሆነው የህወሃት-ኦሮሙማ መራሹ የጎሰኞቹ ስብስብ ተወግዶ በምትኩ ሕዝባዊና አገር ወዳድ መንግሥት በአስቸኳይ እንዲመሠረት ጥሪ እናቀርባለን።

9. አቢይ አህመድ አሊ ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ባለማቋረጥ ያሰለጠነውና እስከ አፍንጫው የታጠቀውን ቁጥሩ ወደ አንድ ሚሊየን የሚጠጋ ዘረኛና እሸባሪው የኦሌልፍ/ሸኔ ሰራዊቱን በማሰማራት፤ በተለይ በኦሮምያ በዋናነት በምስራቅ ወለጋ፣በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ ፤ የሰሜን ሸዋ አዋሳኝ በሆኑ አካባቢዎች አጣዬ፣ ሸዋ ሮቢትና ደራን ጨምሮ በየቦታው በአማራው ወገናችን ላይ ያደረሰውንና እሁንም እየፈፀመ ያለውን ከፍተኛ የሕይወትና የንብረት ውድመት አምረን እንቃወማለን።

10. ኢትዮጵያን በማፈራረስና ጥቃቅን መንደራዊ አገዛዝ ለመመሥረት እንዲረዳቸው የሕወሃት እና የኦሮሞ ነፃ አውጪ ድርጅቶች ዘወትር በሚያላዝኑት ፀረ አንድነትና ፀረ ሰላም የሆነውን ብሔር ብሔረሰብ የጎሰኝነት ትርክታቸው አማካኝነት፤ የአገሪቱን ሕዝብ እርስ በራሱ በቋሚነት በጠላትነት እንዲተያይና እንዲጨፋጨፍ የሚደረገውን ሴራቸውን አጥብቀን እንኮንናለን። ሕዝቡም ይህን ተንኮላቸውን እንዲረዳና እንዳይተባበራቸው ጥሪ እናቀርባለን።

11. የአገራችን የመከላከያና የፀጥታ አስከባሪ ኃይል አባላት፤ ደሞዝህን የሚከፍልህ ከአብራኩ የወጣኸው እናት እና አባትህ መሆናቸውን ከቶም የሚሳንህ አይደለም። መንግስትና የፖለቲካ ስርዓት ቋሚ እንደማይሆኑ በማስተዋል ወገንተኝነትህን ከአብራኩ ከተገኘኸው ሕዝብህ ጎን እንዲሆን ወቅቱ ጥሪ እያቀረበልህ መሆኑን እንዳትዘነጋ እናሳስባለን።

12. በመጨረሻም አቢይ አህመድ አሊንና ሽመልስ አብዲሳን ጨምሮ ሁሉንም ጥፋተኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ እየተደረገ ባለው ሥራ ላይ እንዲተባበሩ ሰባዊነት ለሚሰማው የሰው ዘር ሁሉ እየተማፀንን፤ "ጅራፍ እራሱ ገርፎ፤ እራሱ መልሶ ይጮኸል" እንዲሉ የሕወሃትና የኦሮሙማው ተገንጣይ ኃይሎች እስካሁን የፈፀሙትንና እሁንም በትጋት እየሠሩ ያለውን ወንጀላቸውን ለመደበቅ፤ በተከፋይ ካድሬዎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው አማካኝነት እነኝህ ነውረኞችን ቅዱስ በማስመሰል የሚነዙትን የማደናገሪያ የሃሰት መረጃ፤ በተለይም በውጭ አገር የዜና አውታሮችና በጋዜጣዎች የሚረጨውን፤ የጥቃታቸው ሰለባ የሆነውን ወገን የስም ማጥፋት ዘመቻ፣ በየአገሩ የሚኖሩ አገር ወዳድ ምሑራንና ሕዝባዊ ማህበራት እየተከታተሉ እንዲያጋልጡና እውነቱን ለውጪው ዓለም እንዲያሳውቁ ጥሪ እናቀርባለን።

ኢትዮጵያ አገራችን በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!

አንድነት ኃይል ነው።

የኢትዮጵያውያን ማሕበር በሆላንድ (ኢማሆ)

Postbus 25763,2502 HT 'S- Gravenhage
Tel.031619683890/031652642259 ,Email:info.venholland@gmail.com , bank Nr.NL68INGB0005487444 , **KvK Nummer. 55481345**